# የኢትዩጵያን "የመያዶች አዋጅ" ትክክለኛነት ያረጋገጠው የግብፁ ትዕይንት

**ቶሎሳ ኡርጌሳ-ከአዲስ አበባ**

"If NGO is not NGO…" (መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት /መያድ/ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ካልሆነ…) በሚል ትዝብታዊ የርዕስ መንደርደሪያ ሰሞኑን በአይጋ ፎረም ድረ-ገፅ ያነበብኩትና ግብፅ ውስጥ የሚገኙ "በጎ አድራጊዎች" ያከናወኑት የሚጠበቅ፣ ነገር ግን ማንነታቸውን ነጋሪ ድርጊት ፤አንድ በሀገራችን ውስጥ የተፈፀመ ሁነኛ ክንዋኔ እንደዋዛ በአዕምሮዬን የትውስታ ጓዳ ውስጥ ሽው ብሎ እንዲያልፍ ሳያደርገው የቀረ አይመስለኝም።

…

የትውስታዬ አፅመ-ታሪክ መነሻ የዚያን ሰሞን ሁካታና የገደል ማሚቶ ዓይነት ጩኸት ነው—የዛሬ አራት ዓመት ገደማ። ነገሩ እንዴት መሰላችሁ?!…በነቂስ የህዝብ ይሁንታ "አንተ ትበጀኛለህ! ፤የድህነትንና የኋላ ቀርነትን ቀንበር ከላዬ ላይ አሽቀንጥረህ ትጥልልኛለህ… " ተብሎ የተመረጠው የኢትዩጵያ መንግስት የተጣለበትን አደራ ለመወጣት አንድ ተግባር አከናወነ። የተግባሩ ማጠንጠኛም "በሀገራችን ዴሞክራሲን የሚያጠናክር፣ የኪራይ ሰብሳቢዎችን መረብ በመበጣጠስ ልማታዊነትን የሚያሰፍን እንዲሁም የዜጎችን ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ" ተቀባይነት ያለውና ማለፊያ እሳቤ ነው—"የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ"።

ግና ነገሩ "የሁለት ዓለም" ፖለቲካዊና ርዕዮተ-ዓለማዊ ትግል በመሆኑ፤አዋጁ ከመውጣቱ በፊትና ከወጣበት ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ የሀገራችን መንግስት በገዛ ሀገሩ ውስጥ ህግን የመደንገግ ኃላፊነት እንደሌለው በመቁጠር፤ ሲያሻቸው "በሰብዓዊ መብት ሽፋን"፣ በል ሲላቸው ደግሞ "በዴሞክራሲ ቀኖና" አሊያም "የብዙሃን ማህበራት ታፈኑ" በሚሉ መሰረት የሌለው ስሞታና ውዥንብር የሚንጣጡ ኃይሎች መፈጠራቸው አልቀረም።

እርግጥ የዚህ ፅሑፍ አንባቢ የእነዚህን ኃይሎች "ማንነት" ያጣዋል ብዬ አልገምትም። አዎ! አዋጁ በረቂቅነት እያለና ከፀደቀ በኋላም ቢሆን በሀገራችን ላይ የተቀናጀ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ከፍተው ስላልተሳካላቸው እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ የቅርብ ዘመድ የሞተባቸው ይመስል "እህህ…" በማለት የሚብሰከሰኩ ናቸው—እነዚህ ኃይሎች።

በአዲሲቷ ግብፅ በ"መያድነት" ተደራጅተው ሲሰሩ የነበሩና ሰሞኑን በዚያች ሀገር መንግስት "ከተሰማሩበት ዓላመ ውጭ ሰላምን በማደፍረስ ተንቀሳቅሰዋል" ተብለውም ተወንጅለዋል– "ጉድና ጅራት ከበስተኋላ ነው" እንዲል የሀገራችን ሰው።

ታዲያ በእነዚህ ኃይሎች አንቀሳቃሽ ሞተርነት የሚዘወሩትና "ለትርፍ ያልተቋቋመ" የሚል ስያሜ የተቸራቸው የውጭ "መያዶች" እንዲሁም በገንዘብ ኃይል እንደአሸን የሚፈለፍሏቸው የሀገር ውስጥ "በጎ አድራጊዎችና ሲቪክ ማህበራት"፣ በሀገራችን የውስጥ ፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገቡ ብሎም " እውነተኛ በጎ አድራጊዎች" ሆነው በነጻነት ስራቸውን እንዲያከናውኑ ለማድረግ የወጣውን አዋጅ በጽኑ ሲኮንኑ የነበሩ መሆናቸውን ለአንባቢዎቼ ማስረዳት " ለቀባሪው የማርዳት ያህል" እንዲሉት ዓይነት ይሆንብኛል፡፡

ከሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው የሚባሉት " ዓለም አቀፍ የሪፐብሊካን ተቋም" (IRI)"፣ " የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ተቋም" (NDP) እና " ፍሪደም ሃውስ" የተባሉ የአሜሪካ ተቋማት፣ አባሎቻቸው ከግብጽ ልሳነ-ምድር እንዲወጡ እንዲሁም በወንጀል እንዲከሰሱ ተደርገዋል፡፡ምንም እንኳን የግብጽ መንግስት በወሰዳቸው እርምጃዎች "የረፈደ ነው" የሚያሰኘው ባይሆንም፣በዚያች ሃገር የተካሄደው የኒዮ-ሊበራሊዝም አቀንቃኞች ትዕይንት ግን፣በተለያዩ "የስያሜ ታፔላ" የሚቋቋሙት እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ፣ሲ.ፒ.ጄ ወ.ዘ.ተ ዓይነቶች ምግባራቸውና ዓላማቸው ለየቅል መሆኑን ሰሞነኛው የካይሮ ትዕይንት ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ይፋ ያደረገው ሃቅ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ይህ የግብፅ ትዕይንት " መያዶች" ከመጋረጃው በስተጀርባ ሆነው የሚተውኑትን ድራማ ብቻ ሳይሆን፣እስከ ዛሬ ድረስ ሀገራችንን በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት እንዲሁም በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጆች ዙሪያ የሚያብጠለጥሉበት እውነተኛ ምክንያታቸው ምን እንደሆነም ጭምር የሚያሳይ ነው፡፡ "ስለ ዴሞክራሲ እንሰብካልን" የሚሉት እነዚህ ኃይሎች ሰውነታቸውን ሰደው የአንድን ሃገር ሉዓላዊነት በመጻረር፣አለመረጋጋትን በመፍጠር አሊያም ያልተረጋጋ ህብረተሰብ እንዲኖር በማድረግ የራሳቸውን የኪራይ መሰብሰቢያ ኮሮጆዎችን ለመሙላት በመንግስት ግልበጣ ጭምር የሚሳተፉ መሆናቸው ዋነኛ ዓላማቸው ፖለቲካዊና ርዕዮተ -ዓላማዊ እንጂ "መዝሙረ- ዴሞክራሲ" አለመሆኑን በገሃድ ነግረውናል፡፡

ምንም እንኳን እነዚህ ኃይሎች በተለያዩ የዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ሽፋን በአንድ ሃገር ፖለቲካዊ ክንዋኔ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ከኪራይ ሰብሳቢ ጥቅማቸው አኳያ ለእነርሱ የሚበጃቸውን " ካቢኔ" ለማቋቋም መፈለጋቸው ትላንት የነበረ፣ዛሬም ያለና ነገም የሚኖር " የእኔ አውቅልሃለሁ" አክራሪ ኒዮ-ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ቢሆንም፤ከሃገራችን አኳያ የተከተሏቸው አካሄዶች "በመያዶች አዋጅ" አማካኝነት መክሸፉን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ እንግዲህ ይህ ክስረት ነው—እነዚህን ኃይሎች አብሽቆና ሁኔታው እንደ እግር እሳት ለብልቧቸው በተለያዩ የጥላቻ ታምቡር ድለቃዎች የሃገራችንን ስም ለማጉደፍ ዛሬ እውነተኛ ተግባራቸው እረቃኑን ተገልጦ በታየው " መያድ" ተብዬዎች አማካኝነት እንዲራወጡ የሚያደርጋቸው፡፡

በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ እምነት፤ የዓለም አቀፍ የሪፐብሊካን ተቋም ዳይሬክተርና የአሜሪካ የትራንስፖርት ሚኒስትር ልጅ የሆኑት ሚስተር ሳም ላሁድን ጨምሮ ስምንት አሜሪካውያን፣ ሦስት ሰርባውያን፣ሁለት ጀርመናውያን፣አንድ ኖርዌጂያዊና አንድ ፍልስጤማዊ በአስቸኳይ ካይሮን ለቀው እንዲወጡ የተደረጉበት ትዕይንት፤የመያዶቹንና የአባሎቻቸውን ማንነት ያመላከተ ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ ባሻገርም የኢትዮጵያ መንግስት ያጸደቀው " የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ" ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጧል ማለት ይቻላል፡፡ግና እንዴት?!- ነገሩ ወዲህ ነው፡፡…

" ትንቢት ይቅደም ለነገር" እንዲል መፅሐፉ፤አርቆ አሳቢው የሀገሬ መንግስት የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎችን " ልማታዊ መንግስትን የማኮሰስ" ብሎም የህዝቦችን ሉዓላዊ መብት የመንጠቅ ፍላጎታቸውን ቀድሞ በመረዳቱ፤የኪራይ መሰብሰቢያ መረቦቻቸውን እነርሱ "የበግ ለምድ" ለብሰው በሃሰት ደቀ-መዝሙርነት ከሚዘሙሩለት ዴሞክራሲ፣ ከዜጎች የመደራጀት መብት እንዲሁም ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌ አኳያ በመመልከት አዋጁን ሊያዋጣ ችሏል፡፡ ታዲያ እነዚህ ወሳኝ ጉዳዮች ኒዮ-ሊበራሎች ካሰማሯቸው "መያዶች" አኳያ ከመመልከታችን በፊት ፤ ኪራይ ሰብሳቢዎች ደምስራቸው እስኪገታተር ድረስ ስላበሳጫቸው አዋጅ ጥቂት ማውሳቱ ለግንዛቤ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግስት ያወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይል የተዘጋጀ በመሆኑ፤የሀገራችን ፖለቲካ ከኪራይ ሰብሳቢነትና ከፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ነፃ እንዲሆን የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ

በተጨማሪም አዋጁ በሀገራችን ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ሀገር በቀልና የውጭ በጎ አድራጊ ድርጅቶች በሀገሪቱ የልማት ስራዎች ላይ በስፋት እንዲሳተፉ፣ዜጎች ባቋቋሚቸው ማህበራት ተደራጅተው በንቃት የሚንቀሳቀሱበትን ማዕቀፍ የፈጠረና ወደፊትም የሚፈጥር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ፤ ወትሮም ቢሆን በለመዱት ፀረ-ልማት አቅጣጫ ለመጠቀም የሚፈልጉት የኪራይ ሰበሳቢነት ካምፕ ነዋሪዎች፤ በዚህ የሀገርን እድገት ለማረጋገጥ በተዘጋጀው የህግ ማዕቀፍ መበሳጨታቸው እና መወራጨታቸው የግድ ሊሆን ችሏል፡፡

ምንም እንኳን አዋጁ በርካታ ክፍሎች ያሉት ቢሆንም፤ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በኪራይ ሰብሳቢዎች ካምፕ ውስጥ የሚገኙ የውስጥና የውጭ “መያዶች” መሰል የጎራው ቋሚ ተሰላፊዎች “የምጣዱ ሳለ የእንቅቡ ተንጣጣ” እንዲል የሀገራችን አርሶ አደር ለምን በአሉባልታ ወጀብ እንደሚናውዙ፤ ዓለም አቀፍ እሳቤን ተንተርሶ ከተዘጋጀው አዋጅ አንፃር መመልከት ያሻል፡፡ ለዚህም ዴሞክራሲን፣የመደራጀት መብትንና ከዜግነት ጋር እንዲሁም የመደራጀት መብትና የገንዘብ ምንጭ ያላቸው ተጣምሮ በደምሳሳው መቃኘቱ ተገቢ ነው፡፡

ከጥቅል ኒዩ-ሊበራላዊ አስተምህሮት አኳያ፤ በአፍሪካ ያሉ መንግስታት በአህጉሪቱ ላለው የልማት ችግር መንስኤዎች እንጂ የመፍትሔ አካል አይደሉም ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም በገበያ አክራሪነት ካልሆነ በስተቀር፣በመንግስት ሰፊና የተመረጠ ጣልቃ ገብነት የሚመጣ ልማት የለም የሚል “ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ” ዓይነት ልፈፋውን ያስተጋባል። ታዲያ ይህ አስተምህሮት በልፈፋ ብቻ የተገታ አይደለም–ለመንግስታቱ የሚሰጠውን እርዳታ “በመያዶች” አማካኝነት ማከናወን፤ አንድም የኒዩ-ሊበራል ስርዓት ብቸኛና ለሌሎች የሚቸር፣ ሁለትም ይህን ያልተቀበለ መንግስትና ህዝብ “በበጎ አድራጊዎቹ ድርጅቶች” አማካኝነት ሰለባ እንዲሆን ለማድረግ የሚካሄድ ተግባር ጭምር እንጂ።

እናም ገበያው ያልፈታውን የልማት ችግር ዜጎች “በመያዶች” አማካኝነት እንዲሞሉት ይጠበቃል። በመሆኑም “መያዶች” በአፍሪካ የኪራይ ሰብሳቢ መረቦች በአብዛሃኒት እንዲመሰረቱ ጥረት ያደርጋል። ምናልባትም በአንድ ልማታዊ ሀገር ውስጥ በእነዚህ ኃይሎች የሚደገፉ እንደ “መድረክ” ዓይነት ከሚገኘው ኪራይ ፍርፋሪ ለመቃረም የሚሹ ፓርቲዎች ወይም “ማህበራት” ስልጣን ከያዙ “ተጠቃሚ እንሆናለን” በሚል ለመረቦቹ መስፋፋት ትኩረት ይሰጣል።

ሆኖም ማንም ሚዛናዊ ህሊና ያለው ሰው እንዲህ ዓይነቱ "የኪራይ ሰብሳቢ የብዜት ስሌት" ዴሞክራሲያዊ ብዙህነት ነው ብሎ ያስባል ብዬ አልገምትም። ምክንያቱም ይህን የመሰለ የኪራይ ሰብሳቢነት ፍልሚያ ባለበት ሀገር ውስጥ የቡድኖችን ሽኩቻና የዜጎችን ተጠቃሚነት አጣጥሞ መጓዝ የማይቻል በመሆኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በዚህ ዓይነት መረብ ውስጥ የሚደራጁ ተዋንያን ውስጣዊ ይዘታቸውና አሰራራቸው ከቶም ቢሆን ዴሞክራሲያዊ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም።

ምንም እንኳን የመረቦቹ "የኋላ ደጀኖች" ስለ ዴሞክራሲ "ተግተው የሚፀልዩ" ቢሆንም፤አካሄዳቸው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ስለሆነ፣ የኢትዮጵያ መንግስት በሀገሩ በማበብ ላይ የሚገኘውን ዴሞክራሲ ለማጎልበት "የመያዶችን አዋጅ" ማውጣት የግድ ብሎታል። እርግጥም ዴሞክራሲ ለሀገራችን የህልውና ጉዳይ በመሆኑ፤ የአዋጁ መውጣትን ትክክለኛነት የሚያመላክት ሌላኛው አስረጅ ነው ማለት ይቻላል።

እናም በውጭ ገንዘብና እርዳታ ለመስራት የተቋቋሙት "በጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት" ፤በገንዘባቸው ልክ በተለያዩ ስያሜዎች ከየጎሬያቸው አውጥተው የሚያደራጇቸው ኃይሎች ምክንያት ስር በመስገድ ላይ የሚገኘው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መታወክ ስለሌለበት የአዋጁ መውጣት ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም። ግና የዴሞክራሲ ዘማሪው ኒዮ-ሊበራዝም መልሶ ዴሞክራሲን መደፍጠጡ ምን ይሉት አሰራር ይሆን?...

ያም ሆነ ይህ ግን፤ውድ አንባቢዎቼ በሀገራችን ውስጥ "መያዶች" አይደራጁም እያልኩ እንዳልሆነ እንደምትገነዘቡልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። አዎ! የውጭም ይሁን የሀገር ውስጥ "መያዶች" በኢትዮጵያ ውስጥ ሊደራጁ የሚችሉበት መንገድ እንዳለ ማየት ይቻላል። አዋጁ በግልፅ እንደደነገገው ፤ በተለይም የውጭ "መያዶች" ምናልባትም በሀገራችን ዕድገት ላይ እሴት የሚጨምሩ ከሆነ እንዲሁም በዓለም ላይ ያለውን ዴሞክራሲያዊ እሳቤ ተፃርረው በሀገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ እስካልገቡ ድረስ ተግባራቸውን መከወን ይችላሉ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፤የኒዮ-ሊበራል አስተሳሰብ በየትም ሀገር ውስጥ የሚገኙ "መያዶችን" የሚፈልጋቸው ልክ በአሁኑ ወቅት በግብፅ እንደታየው መንግስትን ለማሽመድመድና ለመተካት ነው— ተጨማሪ የኪራይ መሰብሰቢያ ቋት እንዲሆኑለትም

ጭምር። ግና በጠንካራነቱ የሚታወቀው ልማታዊው የኢትዩጵያ መንግስት እንዲህ ዓይነቱን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በአዋጁ መሰረት አስቀድሞ "ሳይቃጠል በቅጠል" በማለቱ የእኩይ ተግባሩን በር ከርችሞታል ማለት ይቻላል።

በሀገራችን ውስጥ ያለው መንግስት አንድ ልማታዊ መንግስት መስራት የሚገባውን ሁሉ ከማከናወን ወደ ኋላ የሚል አይደለም። ታዲያ ነገሩ "ላም አለኝ በሰማይ..." ዓይነት ካልሆነ በስተቀር፣"መያዶች" የዚህን መንግስት የተመረጠ ጣልቃ ገብነት ሊገድቡ አሊያም አቅሙን ሊያሽመደምዱት አይችሉም። እናም ልማታዊ መንግስት እና ዴሞክራሲያዊ ማዕቀፍ ባለበት ሀገር ውስጥ እነዚህ ኃይሎች "ልማታዊ ቀዳዳን እንሸፍናለን" ማለታቸው ፣ ቀደም ሲል የጠቀስኩት ኪራይ ሰብሳቢዎችን ከማበራከት ውጪ ይህ ነው የሚባል ፋይዳ ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል።

ይሁንና ሁሉም "መያዶች" በጎ ሚና የላቸውም ተብሎ ስለማይታሰብ (ስኬታማ የኤክስቴንሽን ፓኬጆችን በሀገራችን ያስተዋወቀውን "ሳሳካዋ ግሎባል 2000" የተሰኘውን መያድ ያስታውሷል!) ፣ጠቃሚ አስተዋጿቸውን ለማጎልበትና በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል አዋጅ ማዘጋጀትና እነርሱም በዚሁ ማዕቀፍ ስር እንዲንቀሳቀሱ መደረጉ የመንግስትንና "የበጎ አድራጊዎቹን" ተመጋጋቢነት የሚያጠናክር እንጂ ቅራኔ ውስጥ የሚያስገባቸው ሊሆን አይችልም።

በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እምነት፣ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሂላሪ ክሊንተን በሳምንት ጊዜ ውስጥ ብቻ ከግብፅ አቻቸው ጋር ሁለቴ የተገናኙበት እንዲሁም ሌሎች ሁለት የሪፐብሊካን ሴናተሮችና የዋሽንግተን ከፍተኛ ባለ ስልጣናት እንደ ውሃ ቀጂ ካይሮ የተመላለሱበት ዋነኛው ምክንያት ፣ "ቢረፍድበትም አልዘገየም" የተባለው የግብፅ ጊዜያዊ መንግስት "በመያዶቹ" ላይ ያወጣው አዋጅና የመሰረተው ክስ የፈጠረው ስጋት ነው። ሆኖም በየአመቱ ከኦባማ አስተዳደር አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዩን ዶላር የሚለገሰውና ከዚህ ውስጥ አንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዩን ዶላሩን ለጦር ኃይሉ የሚያውለው የዚያች ሀገር መንግስት፣ "እርዳታውን እናቆመዋለን" በሚል ዛቻ ሉዓላዊነቱን መፈታተናቸው እምቁ እውነት የት እንዳለ የሚያሳብቅ ሃቅ ነው።

እርግጥም ተጨማሪ ግዴታዎችን በያዘው የውጭ ኃይሎች ገንዘብ ልገሳና እርዳታ መኖር ለእንዲህ ዓይነቱ ቀጥተኛ ጥቃት ማጋለጡ የሚቀር አይደለም። ለዚህም ነው

የሀገራችን መንግስት "በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ" ላይ፤ ዕድገታችን በራስ አቅም ከሚከናወን ልማት እንጂ፤ ከውጭ በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ መሆን የለበትም በማለት የደነገገው። በመሆኑም በኢትዩጵያ ውስጥ የመደራጀት መብት ህገ-መንግስቱ ለዜጎች ብቻ የሰጠና በዚሁ አግባብ የሚደራጁ "መያዶችም" ከ90 በመቶ የማያንሰው የመንቀሳቀሻ ገንዘባቸው ከሀገር ውስጥ ከተገኘ ምንጭ እንዲሆንና እስከ 10 በመቶ ድረስ የሚሆን ብቻ ገንዘብና ቁሳቁስ የሚያገኙበትን ዕድል ሰጥቷል።

በዚህ ፅሑፍ አቅራቢ አመለካከት፤ የአዋጁ መነሻ የሀገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት ነው። እንደሚታወቀው የፖለቲካ መብቶች ዜጎች ሀገራቸው የምትከተለውን ፖለቲካዊ ሁኔታ ለመወሰን የሚያስችላቸው ስለሆነ ለእነርሱ ብቻ የተሰጠ ነው። ይህን ለመከወን ደግሞ መደራጀት ይኖርባቸዋል። ለዚህም ነው ህገ-መንግስታችን የመደራጀት መብትን በአንቀፅ 31 ላይ በይፋ ዋስትና የሰጠው። ሆኖም ዜጎች ህገ-መንግስቱ የሰጣቸውን መብት ለህገ-ውጥ ዓላማ የሚያውሉት ከሆነ፤ መንግስት የህግ አግባቦችን ተከትሎ የመሰረቱትን ድርጅት ሊያፈርስባቸው ይችላል። ይህ ደግሞ የህግ የበላይነትን የማስከበር ዓለም አቀፍ አሰራር ነው።

በግብፅ ሰሞነኛው ትዕይንት ውስጥ የተመለከትነውና የሀገሪቱ ዜጎች በውጭ ኃይሎች ታግዘው የመሰረቷቸው "መያዶች" ከተቋቋሙበት ዓላማ ውጭ ሲንቀሳቀሱ በመገኘታቸው ዘብጥያ የመውረዳቸው ምስጢርም ይኸው ይመስለኛል። እርግጥ ኒዮ- ሊበራሊዝም በራሱ ሀገር የማይፈፅመውን ፤ለምን በሌሎች ላይ እንደሚያደርግ ለሰሚው ግራ ቢሆንም፤የሀገር ውስጥ "መያዶች" ከታጠሩበት የውሸት ስያሜ አፈንግጠው ህዝቦችን አየቀሰቀሱ ብጥብጥ እንዲፈጥሩ ማሰማራት ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትርጓሜ የሚሰጠው አይመስለኝም። ምክንያቱን አሜሪካን ጨምሮ በርካታ የዳበረ ዴሞክራሲ ያላቸው ሀገራት ፖርቲዎችም ይሁኑ ዜጎች ከውጭ ኃይሎች ለስራቸው ማንቀሳቀሻ የሚሆን ምንም ዓይነት ገንዘብ ተቀብለው ቢገኙ የሚቀጡበትን አሰራር ዘርግተው ሳለ፤ እነርሱ ግን መልሰው በሌላው ቁስል ላይ እንጨት የመስደዳቸው ምስጢር ፍላጎታቸውን በኃይል ከመጫን የመነጨ ካልሆነ በስተቀር ከቶ ምን ሊሆን ይችላል?...

እርግጥም ትክክለኛነቱን በግብፅ ትዕይንት ያረጋገጠው የሀገራችን "የመያዶች አዋጅ" ከዚህ ዓይነቱ ከሉዓላዊነት ጋር ከሚጣረስ የኒዮ-ሊበራሊዝም እሳቤ ታድጎናል ማለት ይቻላል። ያም ሆነ ይህ ግን አዋጁ ለየትኛውም ኃይል ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ ፤

ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ሰዎች የመደራጀት መብት ባይኖራቸውም ቅሉ፤መንግስት ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነትን ባስወገደ መልኩ "የሀገሬንና የህዝባችንን ጥቅም ያስጠብቃል" ብሎ ካመነ መፍቀድ እንደሚችል ያትታል። ታዲያ ይህ እሳቤ በውስጡ መንግስት አስፈላጊነቱን ካላመነበት ፈቃድ አይሰጥም የሚል አንድምታ ያለው መሆኑን ልብ ይሏል።

እንግዲህ ይህ ሁኔታ ነው— የሀገራችንን ሉዓላዊነት ብሎም የህዝቦቿን ፖለቲካዊ የስልጣን ባለቤትነት እንዳይሸራረፍ የሚረዳውን፣ ነገር ግን አዋጁ በወጣ ሰሞን በምናብ ዓለም ራሱን እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በመቁጠር "የሞኝ ለቅሶ" የያዘው ሂዩማን ራይትስ ዎችን ጨምሮ አምንስቲ ኢንተርናሽናል፣ ፍሪደም ሃውስና ሌሎች መሰል "የኪራይ መሰብሰቢያ ማሽኖችን" ያስቆጣው። ምናልባትም ግብፅ ከአምባገነኑ ሆስኒ ሙባረክ ውድቀት ማግስት ሳትዘገይ ይህን መሰሉን አዋጅ ብታወጣ ኖሮ፤ በውስጥ መቆራቆስ የራሳቸውን ፖለቲካዊ ጥቅም ለማጋበስ አሊያም ለሌሎች ለማስገኘት ከሚሯሯጡ "መያዶች" ትድን ነበር ብሎ ማሰብ ይቻል ይሆናል። ሆኖም ግን ከጅምሩ የግብፅን ፖለቲካዊ ትርምስ በመፍጠር ረገድ "የመያዶቹ" እጅ ምን ያህል የረዘመ እንደነበር በእርግጠኝነት መናገር የሚከብድ ይመስለኛል።

የአንድን ሀገር የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳ ላይ ቆሞ እንደ ሀገሪቱ ዜጎች ለመወሰን የሚዳዳው የኒዩ-ሊበራሊዝም እሳቤ ፤የሀገራችን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ በተፀነሰበት ወቅት ሽሉን ለማጨናገፍ መራወጣቸውና ኋላ ላይም በደጋፊ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎቻቸው አማካኝነት የተቀነባበረ የስም ማጥፋት ተግባር ላይ መሰለፋቸው የሚደንቅ አይደለም። እስከ ዛሬ ድረስ "...የኢትዮጵያ መንግስት ለልማቱ ዕገዛ የሚያደርጉለትን መያዶች በአዋጅ እንዲሽመደመዱ እያደረጋቸው ነው..." በማለት የሚያስልፍፋቸው ምክንያትም ሀገራችን እንደ ሰሞነኛዋ ግብፅ በዚህ ዙሪያ ያለባትን ክፍተት በመድፈኗ ያደረባቸው ብስጭት መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው።

ታዲያ እዚህ ላይ የሀገራችን "የመያዶች አዋጅ" ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ፤ህጋዊ በሆነ መንገድ የሀገር ውስጥም ይሁኑ የውጭ ድርጅቶች እንዲንቀሳቀሱ ፈቅዶ ሳለ፣ስለምን በኒዩ-ሊበራሎች የሚዲያ የውሸት ፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ይካሄድበታል? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለኛል። እርግጥ ለምላሹ ሁለት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል።

የመጀመሪያው ኒዩ-ሊበራሊዝም ኃይሎች በተደጋጋሚ በሚነዙት ግዙፍ ፕሮፖጋንዳ አማካኝነት በትራቸውን በማሳየት የሀገራችን ልማታዊ መንግስት አደጋውን ፈርቶ እንዲሸሸና አዋጁን እንዲያስቀር አሊያም ጥቅማቸውን የሚያስከብሩላቸውን ኪራይ ሰብሳቢዎችን በመከላከል የአዋጁን መሰረታዊ ይዘት ለማስቀየር ያለመ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ልማታዊ መንግስትን ለማዳከም ብሎም በአለም አቀፍ ደረጃ ስሙን በማጉደፍ አበዳሪ መንግስታትና ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያቆሙ፣ ካልሆነም እንዲቀንሱ ለማድረግ መሆኑ ግልፅ ነው።

ምንም እንኳን እነዚህ ሁለት ምክንያቶች ከልማት አኳያ የራሳቸውን አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ቢሆኑም፤ከተመሰረቱባቸው የማስገደድ እሳቤ አንፃር ዋነኛና ወሳኝ ጉዳዮች አለመሆናቸውን የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚረዳው እርግጠኛ ነኝ። ለምን ቢባል፤ከኢትዮጵያ መንግስት ባህሪያዊ ማንነት አኳያ ምክንያቶቹ ውሃ የሚቋጥሩ ባለመሆናቸው ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ የኒዩ-ሊበራል ርዕዮት ሰባኪያን እንደሚያስቡት ሳይሆን ፣ የሀገራችን መንግስት እውነትን የያዘ በመሆኑ እንዲሁም ያፀደቀው አዋጅ እነርሱ የሚመሩበትን ዓለም አቀፍ አሰራሮችን የያዘ ስለሆነ ከአቋሙ ፈቀቅ የሚል አይደለም። እስከ ዛሬ ድረስ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለማብጠልጠል የሚሞክሩት አዋጅ ትክክለኛ መሆኑን እያወቁ፣ በሰው የፖለቲካ ሜዳ ውስጥ ገብተው ለመጫወት መፈለጋቸው ላለፉት ሁለትና ሶስት አስርት ዓመታት  ዛሬም “እንደልባችን እንቦርቅባታለን” ከሚል ወልጋዳ እሳቤ እንጂ ሃቁን ስተውት ነው ለማለት አያስደፍርም።

የግብፁ ሰሞነኛ ትዕይንትም የዘህ ፍላጎታቸው ሁነኛ አስረጅ ለመሆኑ ብዙ አዋቂ መሆን የሚጠይቅ አይመስለኝም። ምክንያቱም የኒዩ-ሊበራሎቹ ቀሳውስቶችና “መያዶች” ተቀናጅተው በፕሮፖጋንዳ ናዳ እንደ ግብፁ “እምቢ ካልክ የምንሰጥህን ድጎማ እናቋርጣለን” የሚል ማስፈራሪያ ድረስ መሄዳቸው “ ዓለም ዛሬም በአንድ ዋልታ እሽክርክሪት ውስጥ የምትሽከረከር ስለሆነች እኛን ብቻ ተከተሉ!” የሚል ያረጀና የገረጀፈ ጭላንጭል ተስፋን በመያዝ ጎራውን “ጠብ ያለሽ በዳቦ” ዓይነት ለማካለል እንደሚፈልጉ የሚመላክት በመሆኑ ነው።

ይሁንና የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ሃሰት የፕሮፖጋንዳ ዘመቻል ለመሸሽ ያፀደቁትን አዋጅ የኋሊት የመቀልበስ ታሪ የሌላቸው መሆኑን የፅንፈኛቹ ሃሳባዊ ዘማሪዎች የሚያውቁት አሊያም ሊውቁት የሚፈልጉ አይመስሉም። ታዲያ እኔም ሆንኩ ማንኛውም የሀገራችን ዜጋ ለእነዚህ ኃይሎች "ሃበሻዊ የታሪክ ድርሳናትን አገላብጡ" የሚል ምክር ከመስጠት ውጭ ሌላ የምንለው ነገር አይኖርም።

የፕሮፖጋንዳ ዘመቻውን ከሁለተኛው የሀገራችንን ስም ከማጉደፍ፣ ተቀባይነትን ከማሳጣት እና እርዳታን ከማከላከል ኒዩ-ሊበራላዊ ዓላማ አኳያ ስንመለከተውም "ግቡን መትቷል" ማለት የሚቻል አይመስለኝም። ልምን ቢባል፤ ሌላው ቀርቶ እንኳን "ስም የማጥፋትና ተቀባይነትን የማሳጣት" ዓላማውን ብምንለከት እንኳን ፤ የኢፌዴሪ መንግስት መሪዎች በሚያከናውኑት በሳል ተግባራትና አንድን ነገር አስቀድሞ ከመተንበይ ሁለንተናዊ አቅም በመነሳት ዓለም የሀገራችንንና የመሪዎቿን ስም በደማቅ ቀለም እየፃፈው መሆኑ ነው።

ለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች እንዲሳተፉ (የቡድን 8 እና የቡድን 20 ጉባኤዎችን ያስታውሷል!) በየጊዜው ጥሪ የሚቀርብላቸው ከመሆኑም በላይ፤ አፍሪካን በመወከል የአህጉሪቱ ድምፅ እስከ መሆን ደርሰዋል። በምስራቅ አፍሪካ ውስጥም ሀገራችን በሰላምና መረጋጋት ዙሪያ "የአንበሳውን ድርሻ" በመውሰድ ያላትን ሃላፊነት በብቃት እንድትወጣ በማድረግ ረገድ እርሳቸውና መሪ ድርጅታቸው ወሳኝ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ። በዚህም ሀገራችን በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ የሰላም፣የልማትና የዴሞክራሲ ተምሳሌት ሆና እንድትታይ ማድረግ ችለዋል።

እንግዲህ ከእነዚህ ዓለም አቀፍ ዕውነታዎች በመነሳት የኒዩ-ሊበራሎችና "የመያዶች" ቅንጅታዊ የፕሮፖጋንዳ የተኩስ እሩምታ ዒላማውን መሳቱን ለመረዳት የሚከብድ አይመስለኝም። ግና አንድ መሰረታዊ ሃቅን መገንዘብ ጠቃሚ ይመስለኛል። ይኸውም ኒዩ-ሊበራሊዝም ባለፉት 20 እና  30 ዓመታት የአፍሪካን እምቅ ሃብት በቅኝ ግዛት አጀንዳ ሲዝቅ የነበረና በዚህም ሃብት ያካበተ በመሆኑ እንደ እኛ ባለ በማደግ ላይ ለሚገኝ ሀገር አበዳሪ መሆኑ አይቀሬ ነው። ይሁንና ብድርን የመከላከል ዓላማውን ስንመለከተው ሙሉ ለሙሉ ተሳክቶለታል ማለት የሚቻል አይመስለኝም። ምክንያቱም መንግስት በቀየሰው

የልማት ፖሊሲ ሀገሪቱን ከውጭ ብድርና እርዳታ ጠያቂነት ማላቀቅን እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ነው።

በተለይም ባለፉት ሰባትና ስምንት ዓመታት በሀገራችን ፈጣን እና ተከታታይ ዕድገት መመዝገቡ ብሎም ሀገሪቱ በቀጣዩቹ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ለማሳካት ባቀደችው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አማካኝነት ከተመፅዋችነት ራስዋን ለማላቀቅ ተልማለች። በዚህም ማናቸውንም ልማታዊ ተግባራት ሀገር ውስጥ በተገኘ አንጡራ ሃብት ለማከናወን የሚያስችለውን ዓቅም በሂደት መገንባት እንደሚቻል እሙን ነው። ይህ ሁኔታም ኒዩ-ሊበራሎቹና "መያዶቹ" ብድርን በማስከልከል ተፅዕኖን የመፍጠር ዓላማን የሚገታ መሆኑን የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው እተማመናለሁ።

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ዕውነታን መካድ ያለብን አይመስለኝም። ይኸውም የአንድ ሀገር ዕድገት ስኬታማነት የሚወሰነው ሀገሪቱ ባላት የውስጥ አቅም መሆኑ ነው። እርግጥ የውጭ ድጋፍ ይህን የስኬት ሂደት በማቀላጠፍ ረገድ የማይናቅ ድርሻ ሊኖረው ቢችልም ፤ በወሳኝነት የሀገሪቱ ዜጋ የሚያለማውና የሚፈጥረው ሃብት ነው –የዕድገቱ መሰረት የሚሆነው። በመሆኑም ማንኛውም ዜጋ "የሰው ገንዘብ የሰው ነው" የሚለውን ሀገራዊ ብሂል በማስታወስና "የመያዶቹን" የቅጥፈት ፕሮፖጋንዳ ወደ ጎን በማለት ለሀገሩ ልማት በያለበት አካባቢ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል።

ይህን ማድረጉም እንደ ሰሞነኛው የግብፁ ትዕይንት ሀገራችን የማንንም እጅ ሳታይ በልጆቿ ጥረት ብቻ የኒዩ-ሊበራሊዝምና "የመያዶችን" ውስብስብ የፕሮፖጋንዳ ስንክሳር በቀላሉ እንድትሻገር ያደርጋታል። ያም ሆነ ይህ ግን፤ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ በካይሮ የታየው "የመያዶች" ማንነት የተቋቋሙበት ዓላማ ፖለቲካዊና ርዕዮተ-ዓለማዊ እንጂ ከዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ጋር "ሆድና ጀርባ" መሆናቸውን ቀደም ሲል ለመጠቃቀስ ከሞከርኳቸው መሰረታዊ ሃቆች እንደሚገነዘብ ተስፋ አደርጋለሁ።

እናም ይህ "የመያዶቹ" በጠራራ ፀሐይ እርቃኑን ተጋልጦ የታየው ማንነታቸው ደግሞ፤ የኢትዮጵያ መንግስት ያወጣው "የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት" አዋጅ ትክክለኛ መሆኑን በማሻማ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ነው። ምናልባትም አዋጁ ባይወጣ ኖሮ፤ እነዚህ ኃይሎች ምን ሊፈጥሩ እንደነበር የሚያውቁት እነርሱ ብቻ ናቸው። እኔ ግን

“የቅሌት ምሽት አይነጋም” የሚለውን ሀገራዊ ይትበሃል ለውድ አንባቢዎቼ እያስታወስኩ ፅሑፌን በዚሁ ልቋጭ። ቸር እንሰንብት።